# ማነው ሌባው?

እንግዲሕ ምን ያርገው አልተወለደበት
ስግብግብ ባህሪይ በደሙ የለበት
ክህደት ከናቱ ካባቱ አልወረሰም
ንጹሕ ልብ ነውያለው ለሆዱ አልተግዛም
ድህነት መከራ ችግር ሲመታው
ርሃብ ጥማቱ ህዝቡን ስያውከው
ነገን ለማሳመር ዛሬ የታገለው
ጋሻ መከታችን ወህኒ ነው ያለው

ወገን ተነስ እንጂ ምንድነው ዝምታው
ይህን አሽባሪ ተባብረን እንምታው
ስንቱን አንገላታው ሰንቱን አዋረደው
አይን ባወጣ ክህደት ካገር አባረረው
ዜግነቱን ገፎ ለስደት ዳረገው
ብሔር ብሔረሰብ ብሎ ከፋፈለው
ሌት ተቀን ሲለፋ ኑሮን ለማሸነፍ
ባለጌ አዘዘበት ቀን በቀን የሚዘርፍ

-------

*(ግጥም - ዮሴፍ ይፍሩ)*

ኢትዮሚድያ - Ethiomedia.com
February 5, 2012